ለተሻለ ተጠቃሚነት በጋራ መልማት

*“የግብጽና የኢትዮጵያ ግንኙነት ለፍቺ የማይመች ጠንካራ ጋብቻ ነው።”*

አቶ መለስ ዜናዊ

*“ፈጣሪ አንድ ውኃ እንድንጠጣ ስላደረገን ያለን አማራጭ ተሳስቦ መኖር ነው።”*

ፕሬዚዳንት አል ሲሲም

ስሜነህ

ከውኃ አጠቃቀም አንፃር “ትብብር” ማለት በጋራና በተቀናጀ መልኩ በአካባቢ፣ በብሔራዊ፣ በክልላዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ውሃውን ማስተዳደርና መጠቀም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የናይል ተፋሰስ ሃገሮች ራሳቸውን ለትብብር ክፍት ለማድረግ የሚያስገድዱ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ከነዚህ መካከልም በሕዝብ ቁጥር ዕድገት፣ በተጨማሪ የውኃ ጥያቄ፣ በውኃ ገብ አካባቢዎች መመናመን፣ በውኃ ጥራት መቀነስ የሚጠቃው አካባቢ ትብብርን የሚሻ መሆኑን የሚገልጸው ጥናት የመጀመሪያው አስረጅ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የውኃ አስተዳደር ላይ የጋራ ስምምነት መጥፋቱ ከሰላምና ደኅንነት ጋር የተያያዙ ውጥረቶችን ማንገሱም የሚጠበቅ እንደሆነም ጥናቶቹ ያረጋግጣሉ።

የበርካታ ወንዞች ባለቤት የሆነችውና የአባይ ወንዝ ባለንብረት የሆቸው ኢትዮጵያ ሃይል በማመንጨት በኩል ያለችበት ደረጃ ገና የሚባል ነው። የአባይ ባለቤት እንደመሆናችን ዓባይን አትንኩብኝ ስትል ለዘመናት ከቆየችው ግብጽ አንፃር ስንለካ በርግጥም ያለንበት ደረጃ የሚያሳዝን ነው፡፡ ዛሬ ላይ በረሃይቱ ግብጽ 27 ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ስታመነጭ የወንዞች መናሃሪያ የምንባለው እኛ ግን ገና 4ሺህ ምናምን ላይ ነን፡፡

ስለሆነም የአባይ ባለቤት እንደመሆናችን ከማንምና ከምንም በላይ ልንጠቀም ግድ ይለናል። ምንም እንኳ ደረጃው ቢለያይ በአባይ ላይ መብት ያላቸው ሃገራት በሙሉ ከአባይ የመጠቀም መብታቸውም እንዲሁ የተጠበቀና ማንም ሊቸራቸውና ሊነሣቸው የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

የአባይ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ በአባይ ላይ አንዳች ነገር እንዳትሠራ ግብጽ ላለፉት በርካታ አመታት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንቅፋትነቷን በተግባር ያሳየች ከመሆኑም በላይ በተለይም ካለንበት ድህነት አኳያ በውጭ በምንጠብቃቸው የፋይናንስ ምንጪቻችን ላይ ተነግሮ በማያልቅ ውትወታዋ ፕሮጀክቶቻችንን ሁሉ ስታጨናግፍ ኖራለች፡፡ ይህ ታሪክ ዛሬ በአል ሲሲ እየተቀየረ ያለ ይመስላል።

ከ28ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም እና ፕሬዚዳንት ኤል ሲሲ የተናጠል ውይይት አድርገዋል። ሁለቱ መሪዎች በአምስት ነጥቦች ላይ ውይይት በማድረግ የጋራ አቋም ይዘዋል። መሪዎቹ በሀገራቱ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጠናከር እስካሁን የተገኙ መልካም ዲፕሎማሲያዊ ድሎችን ለማጉላት እንደሚጠቅሙና የሁለትዮሽ መተማመንን ለመፍጠር እንደሚያግዝ ተስማምተዋል።

ሁለትዮሽ ቀጠናዊ የትብብር መስኮችን ማስፋት እና ማጠናከር በተለይም በፖለቲካ፣ ሰላምና ፀጥታ፣ በኢኮኖሚ ዘርፍ ያሉ ትብብሮችን ማጉላት፤ ሁለትዮሽ ግንኙነትና ወንድማማችነትን የሚጎዳ ማንኛውንም አይነት ክስተት መቆጣጠርና መገደብ እንደሚገባም ነው ከስምምነት ላይ የደረሱት። ታላቁ የህዳሴ ግድብን አስመልክቶም የሶስትዮሽ የቴክኒክ ኮሚቴ ውይይቶችን እየተከታተለ እንደሆነና ግድቡን አስመልክቶ ያላቸውን  በትብብር መንፈስ የመስራት ቁርጠኝነትን አድሰዋል።

የመረጃ ልውውጥን ማሳደግ፣ የሁለትዮሽ ግንኙነትንና የጋራ ጉዳይ በሆኑ ቀጠናዊ እና አለማቀፋዊ ጉዳዮች በመሪዎች እና በተቋማት ደረጃ ተከታታይነት ያለው ምክክር እንዲካሄድም፤ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና በህዝቦች መካከል መተማመንን ለማሳደግ እንደሚያስፈልግ ለዚህም የመገናኛ ብዙሃን  ወሳኙን ሚና መጫወት እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም እና ፕሬዚዳንት ኤል ሲሲ ተስማምተዋል።

መሪዎቹ በቋሚነት በተለያየ ጊዜ በሁለቱ ሀገራት ጉብኝት እንደሚያደርጉም ከመግባባት ላይ ደርሰዋል። በዚህ አጋጣሚም ፕሬዚዳንት ኤል ሲሲ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም በቅርቡ በግብፅ ጉብኝት እንዲያደርጉ ጋብዘዋቸዋል።

የትኛውም ሃገር ከሃገራት ጋር በሚኖረው ግንኙነት መነሻው የራሱን ጥቅም ማስጠበቅ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ስለሆነም የተፋሰሱ ሃገራት በሙሉ ከድህነት ለመውጣት በሚያደርጉት ጥረትና ዘላቂነት ላለው ልማት የሚያዋጣቸው ተፈጥሮ በቸራቸው ሃብት በጋራ መጠቀም ብቻ እንደሆነ ግብጽ የገባት ይመስላል ።

ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ለተፋሰሱ ሃገራት ሁሉ የተሻለ ጠቀሜታ እንዳለው በተለይም ለግብጽና ሱዳን ደግሞ የላቀና ዘለቄታዊነት ያለው ፋይዳ እንዳለው ከቀደሙት የግብጽ መንግስታት ይልቅ አልሲሲ እየገባቸው የመጣ ለመሆኑ ከላይ የተመለከተው ሰሞንኛ መረጃ አመላካች ነው።

በአንፃሩ የሱዳኑ አልበሽር በትብብር ስለመልማት ያሳዩት ቁርጠኝነት ግብጽንም ወደዚሁ እና ጠቃሚ ወደሆነው መስመር እንድትገባ የገፋት ይመስላል። በዚህም ተባለ በዚያ ግን የግድቡ መገንባት በተፋሰሱ አገራት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ አለመኖሩ በኢትዮጵያ በኩል ቀድሞ የታወቀና በጥናት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የማረጋገጡ ጉዳይም የተከናወነው ኢትዮጵያን ጨምሮ ቅሬታ አለን ሲሉ በነበሩት ሀገራትም ነው። በሶስቱ የተፋሰሱ አገራት(ኢትዮጵያ፤ ግብፅና ሱዳን) ትብብር  የተመራው ይህ የአዋጭነት ጥናት በነሱ ይሁንታ ከተመረጡና ከየአገራቱ የተውጣጡ ስድስት ባለሙያዎችና በሶስቱ አገራት በጋራ የተመረጡ አራት ዓለም ዓቀፍ ባለሙያዎችንም ያካተተ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚህም የታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ የጥናትና የዲዛይን ሰነድን በመመርመር፣ በግንባታው ቦታ በመገኘትና ሂደቱን በመቃኘት፣ በሶስቱ አገሮች ውስጥ ለስድስት ጊዜ ያህል በመሰባሰብና በተነሱ ጉዳዮች ላይ በመወያየት እንዲሁም ከግድቡ የግንባታ ተቋራጮችና አማካሪዎች ጋር በመመካከር የደረሰበትን የመጨረሻ የጥናት ውጤት ለሶስቱም  ሃገራት ማቅረቡ ይታወሳል፡፡

በዚህም የኢትዮጵያ የታላቁ የህዳሴ ግድብ የዲዛይን ስራ አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ የዲዛይን መመዘኛና መርሆዎች ላይ የተመሰረተ፤ ለሶስቱም አገራት ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ፤ እንዲሁም በሁለቱ ተጋሪ አገራት(ግብፅና ሱዳን) ላይ ጉልህ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን ቡድኑ በጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በተፋሰሱ አገራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያስከትል፤ በአንፃሩ ልማትን የሚያፋጥን ታላቅ ፕሮጀክት መሆኑም ተመልክቷል፡፡ ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይልን በማመንጨት  የኃይል ፍላጎትን ለማሟላት የጀመረችው ጤናማ አካሄድ አንዱ አካል መሆኑንም ጭምር የሚያረጋግጥ ጥናት እንደሆነ አሁን ለአልሲሲ ግልጽ የሆነ ይመስላል፡፡

ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ  በህይወት ዘመናቸው "የግብጽና የኢትዮጵያ ግንኙነት ለፍቺ የማይመች ጠንካራ ጋብቻ ነው" ማለታቸውንም አልሲሲ ያስታወሱ ይመስላል።   ፕሬዚዳንት አል ሲሲም "ፈጣሪ አንድ ውኃ እንድንጠጣ ስላደረገን ያለን አማራጭ ተሳስቦ መኖር ነው" ያሉትን ቃል ያከበሩ ይመስላል ።